የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

ጥቅምት 25/2002

## ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ መፈክር አሁንም ወቅታዊ ነው!

የወያኔ ቡድን ለሥልጣን ከበቃ ጊዜ ጀምሮ ብዙ ሺ ዜጎችን አፍኖ አስሯል፤ ደብዛቸውን አጥፍቷል። አንድም የፖለቲካ እስረኛ የለም ብሎ ሽምጥጦ እየካደ ሺዎችን ግን በጉድጓድ እስር ቤቶችናማጎሪያ ቤቶች ከቶ ሲያሰቃይ ዓመታት አልፈዋል። ከቃሊቲ እስከ ደጀና-- ቃሌማ፤ ፃኢና መቀሌ ብዙ ሺ ዜጎች ፍዳን ተቀብለዋል፤ ዛሬም በመሰቃየት ላይ አሉ። የቀደሞው አገዛዝ ደጋፊዎች በሚል፤ የወልቃይት፤ፀለምት፤ ጠገዴ ወዘተ  አማፅያን በሚል፤ የኢሕአፓ ደጋፊዎች በሚል፤የተቃዋሚ ድርጅቶች አባሎች በሚል፤ በ1997 ኡ ምርጫ ተቃዋሚ ድርጅቶችን ደገፋችሁ በሚል ብዙ ሺዎች በየጉድጓድ እስር ቤቶች፤ በሸዋ ሮቢት፤ዴዴሳ፤ ዝዋይ፤ ብር ሸለቆ ወዘተ ታፍነው መከራን እየተቀበሉ ናቸው። ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ናቸውና በአስቸኳይ ይፈቱ ብሎ መጮህ መታገል ወቅታዊና ተገቢ ነው።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ አንድም ሰው በፖለቲካ ተቃውሞ ምክንያት የታሰረ የለም ሲልና በእስር ቤት ያሉ ወንጀለኞች እንጂ በፖለቲካ ጉዳይ የታሰሩ አይደሉም ብሎ ሲክድ በሌላ በኩል ደግሞ ተቃዋሚ ሀይሎች ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ የሚለውን መፈክር እንዲተዉና በየፊናቸው የእኛ ለሚሏቸው ብቻ እስረኞች እንዲጮኹ ለማድረግ ሲያሴርና ሲጥር ጊዜ አልፏል። ይህን ሴራ ተቀብሎ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ጥሪን ወደ ጎን ማድረጉ/መተዉ ስህተት መሆኑን ኢፖእአኮ እንደገና መጠቆም ይፈልጋል። የ “ እኛ” ከተፈቱ ለሌላው ምን ገዶን የሚለው አቅዋም የሚያስወግዝ ነው። አበራሽ ስንል ብርቱካን፤ ፀጋዬ ስንል ወንዱ ሲራክ፤ የኢሕአፓ ስንል የኦነግ፤ የጋምቤላ ስንል የኦጋዴን፤ የሰሞኑ ስንል የቆዩትና ፍትህ ያላገኙት የቀደሞዎቹን ማንሳት አለብን። ሰብዓዊ መብት ይከበር ስንል በተሸራረፈመልክና  ለተወሰኑቱ ሳይሆን ለሁሉም ነው/መሆን አለበት። ስለዚህም ኢፖአአኮ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ የሚለው አቅዋም ወቅታዊና ትክክል ነውና ሁሉም ድርጅቶችን ይህን መፈክር መፈክራቸው እንዲያደርጉ ጥሪ ያስተላልፋል። የወያኔ ቡድን በሚወሰንልን ክልል አንግባ ። የ “ እኛ” ወገን እስረኞች ሁሉም የታሰሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው ።
ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ!!

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE